4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681

ቁጥር _186/2000____
ቀን ሚያዝያ ፳፰፣ ፳፻
Date 05/06/2008

"የማይገለጥ የተከደነ፥ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለም" (ማቴ 10፡ 26)።

# ምኞት ወይስ ቅዠት

## ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የተላለፈ አጭር መግለጫ፤

የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የቀደሙ አባቶቻችን ከመንፈስ ቅዱስ አግኝተው ያስረከቡንን ውሳኔ (ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን) መሠረት ያደረገ ነው እንጅ የዘመናችን ካባ ለባሽ ፖለቲከኞች እንደሚያምኑት በግለሰቦች በጎ ፈቃደኝነት ወይም በድርድር የሚከናወን የፖለቲካ አጀንዳ አይደለም።

አንድ ሕጋዊ ፓትርያርክም የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ መሆኑ መጠን ከዚህ የተለየ ድብቅ ዓላማ ሊኖረው አይችልም።

ሐቁ ይህ ሆኖ ሳለ "ኢትዮጵያ ዛሬ" የተባለ ድኅረ ገጽ ዓርብ ሚያዝያ ፳፬ ቀን ፳፻ ዓ.ም. (May 2, 2008)፣ "ስደተኛው ፓትርያርክ ለእርቅ ወደ ኢትዮጵያ ሊሄዱ ነው" በሚል ርዕስ ያሰራጨው የፈጠራ ጽሑፍ ብዙዎችን ግራ ያጋባ የሰሞኑ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ እንደ ሰነበተ መገንዘብ ችለናል።

ስለዚህ ይህ ዓይነቱ ወሬ ተራ አሉባልታ መሆኑ ቢታመንም ከምዕመናን ጆሮ ከደረሰና ከተስፋፋ ዘንድ ማስተባበል የግድ በመሆኑ ቅዱስ ሲኖዶስ የሚከተለውን አጭር መግለጫ አውጥቷል።

1. በመሠረቱ የዕርቅ ጉዳይ ከተነሳ ዘንድ ዓለምአቀፍ የሆነውን የቤተ ክርስቲያን ቀኖና የጣሰው ክፍል ጥፋቱን አምኖ ከተጸጸተና ለቤተ ክርስቲያናችን ደኅንነት፣ ለሀገራችን ዕድገት የሚበጅ፣ ለሕዝባችን ነጻነት የሚያመጣ እውነተኛና መሠረት ያለው ብሔራዊ የዕርቅ መድረክ ከተከፈተ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ለውይይት በሩን ክፍት አድርጎ የሚጠባበቅ መሆኑን በጽናት ያረጋግጣል።

2. እነዚህ ነገሮች ባልተሟሉበትና በሀገር ውስጥ ባሉት ፖለቲከኞች ዘንድ ለዕርቅ የተዘጋጀ አእምሮ በሌለበት በአሁኑ ሰዓት፣ "ኢትዮጵያ ዛሬ" የተባለ ድኅረ ገጽ የበተነው ይህ የፈጠራ ጽሑፍ ታማኝነትና መሠረት የሌለው፣ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ያልመከረበት፣ ለእውነት የቆሙ ኦርቶዶክሳዊያንን ግራ ለማጋባት ፖለቲከኞች ከአእምሯቸው አመነጭተው የበተኑት የማደናገሪያ ፕሮፓጋንዳ

4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681



መሆኑን ምዕመናን አውቀው በአልተረጋገጠ ወሬ ግራ እንዳይጋቡ ቅዱስ ሲኖዶስ ይመክራል።

3. ከባለሥልጣኑ ወይም ከሚመለከታቸው አካላት ፈቃድ ሳያገኝ የአንድን ፓትርያርክ ፎቶ በራሱ ፈቃድ በግል ድኅረ ገጹ ላይ ለጥፎ ተጨባጭነት የሌለው የማደናገሪያ ጽሑፍ የበተነው "ኢትዮጵያ ዛሬ" (http://www.ethiopiazare.com/) የተባለው ድኅረ ገጽ ባለቤት በፈጸመው የድፍረትና ሕዝብን የማደናገር ተግባር በሕግ የሚጠየቅ መሆኑን ቅዱስ ሲኖዶስ ያረጋግጣል።

በመጨረሻም ይህ ነገር አንገብጋቢ የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ መሆኑ ገብቷችሁና አሳስቧችሁ፣ በስልክ፣ በኢሜልና በፋክስ ሐሳባችሁን ስትገልጹ ለቆያችሁ በዓለም ዙሪያ ላላችሁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ቅዱስ ሲኖዶስ ከልብ የመነጨ ምስጋናውን ያቀርባል።

እግዚአብሔር አምላክ ለሀገራችን ሰላምን፣ ለሕዝባችን ፍቅር አንድነትን ይላክልን፣ አሜን።

ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ